አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 8

የካቲት 27 ቀን 2014ዓም (06-03-2022)

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል ከትናንትና በስቲያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ የብጹዕ አቡነ ማርቆርዎስን ዜና እረፍ በመስማቱ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ለመግለጽ ይወዳል።በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ለኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አባቶችና ምዕመናን ብርታትና መጽናናትን ይመኛል።

የዛሬው የእሁድ የዬካቲት 27ቀን 2014 ዓም ወይም የማርች 6- 2022 አገር እንዴት ሰነበተች ዓምዳችን የተለያዩ እርእሶች የሚዳስስ ይሆናል።

ካለፈው እሁድ ስንነሳ ዋናና አንገብጋቢ ሆኖ ትኩረት ተሰጥቶት ሕዝቡን ያነጋገረው ጉዳይ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የአማራውን የመብት ትግል ለመቅጨት ባወጣው መመሪያ በጎጃምና በጎንደር፣ በሸዋና በወሎ ሕዝብ ድጋፍና ተሳታፊነት የሚንቀሳቀሰውን የአማራ ፋኖና ልዩ ሃይል ለማኮላሸት አቅዶ ያልተሳካለት እርምጃ መውሰዱ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአማራው ማህበረሰብ ላለፉት 30 ዓመታት የሰፈነውን ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አማራ የሆነ አገር ጠል ቡድን ከመታገል ተቆጥቦ አያውቅም።በትግሉም ብዙ መስዋእትነት ከፍሏል።ልጆቹ ተገለዋል፣ቆስለዋል፣ ታስረዋል፣ተሰደዋል።በተለይም ላለፉት አራት ዓመታት የተረኛው የኦሮሙማ ቡድን ሥልጣኑን ከጨበጠ ወዲህ ግፍና በደሉ ይበልጥ ተጠናከረ እንጂ አልቀነሰም።በጣም የሚያሳዝነው ላለፉት ሰላሳ ዓመታት በስሙ የሥልጣን ተካፋይ የሆኑት የራሱ ልጆች የሚያደርሱበት በደልና መከራ ነው።የአማራው ማህበረሰብ ከሌሎቹ ወገኖቹ ጋር ተባብሮ ለ27 ዓመታት ኢሕአዴግ በሚል ጭንብል ሥልጣን ላይ የተቀመጠውን ዘረፊና ፋሽስታዊ ወያኔ መራሽ ቡድን ከስልጣን ቢያባርርም ለከፈለው መስዋእትነት ያገኘው ትሩፋት ቢኖር ሥልጣኑን ጠቅልሎ በያዘው የኦሮሙማ ቡድን ካለፈው የባሰ ግድያ፣መቁሰል፣መዘረፍ፣መፈናቀልና መሰደድ ነው።የግፍና በደሉ ዋንጫው ሞልቶ ሲፈስ በሕግ ሊያገኝ ያልቻለውን መብቱን ለማስከበር ጠመንጃ አንስቶ ለመታገል የተሰለፈው ሕዝባዊ ሃይል ወያኔን በጠራረገበት ክንዱ ተረኛውንም እንዳይጠራርገው ብርክ የለቀቀበት የኦሮሙማ መራሹ ብልጽግና ቡድን በአንደኛ ደረጃ ጠላትነት ፈርጆት ለማጥፋት በመንቀሳቀስ ላይ ነው። በባሕርዳርና ጎንደር የጀመረው የማፈን ሙከራ በሕዝቡ ተቃውሞ ሳይሳካ የቀረ ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ሙከራው ቀጥሏል።

አማራው አያት ቅድመ-አያቶቹ የኖሩበትን እሱም ተወልዶ ያደገበትን የራያና አዘቦ፣የወልቃይትና ጠገሌን መሬት ተነጥቆ ባገሩ ባዕድና ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ ላለፉት 45 ዓመታት ኖሯል።ከአራት ዓመት በፊት ወያኔ ተወግዶ መቀሌ ሲገባ የትግሉ ፍሬ የሆነውን ያባቶቹን መሬት በእጁ መልሶ ሊያስገባ ችሏል። ይህ ያልተዋጠላቸው የወያኔና በአብይ አህመድ አሊ የሚመራው የኦነግ አገር አፍራሽ ሃይሎች በጥምረት አማራውን ከራሱ እርስት ዳግመኛ ለማባረርና የእርቅ መደራደሪያ ለማድረግ መንቀሳቀስ መጀመራቸው በግልጽ ታይቷል።በሥልጣን ሽኩቻ የተዋጉት የወያኔና የኦነግ መራሹ ቡድኖች ጠባቸውን ወደጎን ትተው መሣሪያና መረጃ እዬተቀባበሉ በጋራ ጠላታቸው በሆነው የአማራ ማህበረሰብ ላይ ጦራቸውን በማሰማራት በተለያዩ አቅጣጫዎች ጥቃት ቢከፍቱበትም የአማራው አይበገሬ ከተመሳሳይ ጥቃት ከደረሰበት የአፋር ወንድሙ ጋር ሆኖ እዬደጋገመ የመጣባበትን ጠላት ጦር ድባቅ እዬመታ መለሰው።አለ የተባለው ያገሪቱ መከላከያ ጦርነቱ ተጠናቋል በሚል ፌዝ ከዳር ቆሞ

ከመመልከት ባሻገር ግዳጁን አልተወጣም።የአፋር ሕዝብ የመከላከያ ሃይሉን እርዳታ ሲጠይቅ ጆሮ ዳባ ልበስ ተባለ።ብቻውን እንዲጋፈጥ ተፈርዶበት ብዙዎች ሞቱ፣ንብረት ወደመ፤በሽዎች የሚቆጠሩም ተፈናቀሉ።ከጎኑ የተሰለፈው የአማራ ፋኖ ብቻ ሆነ።የመንግሥቱ ቸልተኝነት በእልህና በቁጭት የመዋጋት ወኔውን ከፍ አደረገው እንጂ አላንበረከከውም።በማእከላዊው መንግሥት ድጋፍና ትብብር በተደጋጋሚ ከቦ ጥቃት ለማድረስ ዕድል የተቸረው ወያኔ እስከ አሁን ድረስ ማጥቃቱን አላቆመም። የተወሰኑ ቦታዎችንም ተቆጣጥሮ ያልያዘውን ለመያዝ ሙከራ እያደረገ ይገኛል። ኦሕዴድ መራሹ ቡድን የአዲስ አበባው የሥልጣን መንበሩ ለአደጋ እስካልተጋለጠ ድረስ ደንታ እንደሌለው በአማራውና በአፋሩ ላይ ያለው አቋም አረጋግጧል።

የአማራውም ሆነ የአፋሩ ጥያቄ ከሚኖርበት መሬት በላይ በሆነው በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ነው።ይህ የማይዋጥላቸው ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ስብስቦች አማራውንና ሌላውን በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረውን ዜጋ ሁሉ ለማጥፋት ቆርጠው ተነስተዋል።የራስ ምታት የሆነባቸውን የአማራ ፋኖ፣ ሚሊሽያና ልዩ ሃይል ለማዳከም ያልጠነሰሱት ሴራ የለም።መሪ ናቸው የሚባሉትን በመደለልና በማስፈራራት ብሎም ከሥልጣን በማሶገድ፣እምቢ ያሉትንም በማሰርና በማሳደድ ትግሉን ለማኮላሸት ሞክረዋል፤ እዬሞከሩም ነው።የወልቃይትን ሕዝባዊ ኮሚቴና ልዩ ሃይል ለማዳከም ሲባል የጦር መሪ የሆኑትን የልዩ ሃይል አባላት ከቦታው ተሰስተው ወደ ደሴ እንዲሄዱ ከብልጽግና ተብዬው ትዕዛዝ ደርሷቸው እምቢ ብለዋል።አብይ አህመድ የሚመራው ብልጽግና በቅርቡም የአማራው የልዩ ሃይል አዛዥ የሆነውን ብርጋዴር ጄነራል ተፈራ ማሞን ከቦታው አንስቶ በቢሮ ውስጥ ተከርችሞ እንዲቀመጥ ቢያዝም፣ተንኮሉ የገባው ጄነራል በሹመት ስም የሰጡትን የቁም እስራት እምቢ ብሏል።ጄነራሉ አከታትሎም በወያኔና በሥልጣን ላይ ባለው የኦሕዴድ መራሹ ቡድን መካከል ያለውን ትስስር፣ የመከላከያ አዛዦችን ደባና ተንኮል ዝክዝክ አድርጎ ከሜዳ ላይ ዘርግፎታል።ይህም ለነአብይና ለመሰሎቹ በተለይም በአማራው ስም ሥልጣን ላይ ላሉት የብአዴን መሪዎች የቂጥ ላይ ቁስል ሆኖባቸዋል።ቀደም ሲል የብልጽግናው የሥራ አስፈጻሚ አባል አቶ ጸጋዬ አራጌ ካወጣው የዘረፋና ሌብነት ምስጢር የማጋለጥ እርምጃ ጋር ይህ የጄነራል ተፈራ ማሞ ሲጨመርበት የሥርዓቱን ወንጀልና ዓላማ በማያሻማ መልኩ ወለል አድርጎታል።

የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም እንዲሉ የኦሕዴድ -ኦነግ መራሹ ቡድን በስርቆት ላይ ስርቆት፣በዘረፋ ላይ ዘረፋ፣በማሰር ላይ ማሰር፣በማፈናቀል ላይ ማፈናቀል ፣በማሳደድ ላይ ማሳድዱን ፣በቅጥፈት ላይ ቅጥፈት፣በክህደት ላይ ክህደቱን ተያይዞታል።መንግሥታት ሁሉ መውደቂያቸው ሲቃረብ ቀልብ ይነሳቸዋል።ያብዳሉ።እብድ ደግሞ ከለቀቀት ጥፋት ያጠፋል፣ የያዘውን ይሰባብራል።እነዚህም የሥልጣን እብዶች የያዙትን አገር እንዳይሰባብሩ በጊዜው መፈናፈኛ እንዳያገኙ ማድረግ ተገቢ ነው። አገርና ብርጭቆ አንድ ነው፤አያያዝ ይጠይቃል።ከእጅ ካመለጠ አይተርፍም።የሚንከባከበው ባለቤት ይፈልጋል። ለኢትዮጵያ ባለቤቷ ሕዝቡ ነው፤ሕዝቡም የጋራ አገሩን ለማዳን በጋራ ሊቆም ይገባዋል። ጠላቶቹ በተንኮልና በጉልበት ሥልጣን ላይ እንደወጡት ሁሉ ከሥልጣናቸው በሰላም አይወርዱም። ደም ከማፍሰስ አይመለሱም።ያንን ለመቋቋምና የድሉ ባለቤት ለመሆን ከራሱ ተውጣጥቶ ትግል የጀመረውን ሕዝባዊ ጦር በስንቅ፣በትጥቅ፣በመረጃ፣በገንዘብና በፕሮፓጋንዳ ማጠናከር ተገቢ ነው። መብትና ነጻነት፣የአገር ልዑላዊነት በጥቂቶች መስዋእትነት ብቻ አይገኝም።ጥቂቶች ይጀምሩታል፣ ብዙዎች ይፈጽሙታል። ስለሆነም ሁሉም አገሩን የሚወድ፣የዴሞክራሲ ስርዓትና ፍትሕ እንዲሰፍን የሚሻ፣ ኋላ ቀር የጎሳ ፖለቲካን የሚጠዬፍ፣በዓለም ከታወቀበት የርሃብና የስደት ኑሮ ለመገላገል የሚፈልግ፣ታሪኩን ለማደስ የሚመኝ፣በአገር ማዳኑ ትግል ውስጥ መሳተፍ ወይም የሚችለውን ማበርከት ይጠበቅበታል።

ወደ ሌላው ጉዳይ ስናመራ ባለፈው ሰንበት ለሁለት ቀናት በዝግ የተካሄደው የኦሕዴድ -ኦነግ መራሹ ብልጽግና የስራአስፈጻሚ ስብሰባን የሚመለከት ይሆናል።ስብሰባው ዝግ ነው ቢባልም ስብሰባው ሳይጠናቀቅ ስለውይይቱ አፈትልከው የሚወጡት መረጃዎች ከሕዝቡ ጆሮ ለመድረስ ችለዋል።የስብሰባው ዓላማ ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቀርብ የውይይት ሰነድ ላይ ለመወያዬት ነበር። የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ  ለሚቀጥለው ብሔራዊ የምክክርና የውይይት ሂደት ለመዘጋጀት የሚረዳ ነው ቢባልም  ስብሰባው በንትርክና በመወነጃጀል ተጀምሮ የተጠናቀቀ ሆኗል።ለፍጥጫውና ንትርኩ ምክንያት የሆነው ከቀናት በፊት በአመራር ላይ ባሉት አባላት በተፈጸመ ስርቆት ላይ የወጣው አጋላጭ መረጃ  እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ስብሰባውን የመራው አብይ አህመድ በቁጣና በንዴት  ስሜት የአባላቱን መብት በተዳፈረ መልኩ ፣በማስፈራራትም ጭምር አምባገነናዊ ማንነቱን ያሳዬበት ስብሰባ ነበር። በስብሰባው ላይ ባልታወቀ ምክንያት ሶስት የአማራው ብልጽግና(ብአዴን) አመራሮች አቶ ገዱ አንዳርጋቸው፣አቶ  ዩሃንስ ቧ ያለውና አቶ ላቀ የያሌው አልተገኙም።በስብሰባው ላይ ስለጦርነትና ስለ አማራው እልቂት በአጀንዳ የተያዘ ባይሆንም ከተገኙት  የአማራው ብልጽግና አባላት መካከል አቶ ዓለሙ ጀንበሬ የተባለው ምንም እንኳን የጥያቄ መንደርደሪያ ያደረገው ከመንግሥቱ ሃይለማርያም ጀምሮ እስከ አብይ ድረስ  በማሞገስ ቢሆንም አያይዞ በራያና በወልቃይት ዙሪያ ጥያቄ አንስቷል። ሌሎቹ አቶ ጸጋ አራጌ፣አቶ ጃንጥራር አባይና  አቶ  ቀለመወርቅ ስለአማራው መበደልና መጨፍጨፍ በድፍረት ጥያቄ ቢያቀርቡም ሌሎቹ  ደመቀ መኮንንን ጨምሮ  ምላሳቸውን የዋጡ ይመስል በፍርሃት ሲቁለጨለጩ ታይተዋል። የተቁነጠነጡት የሥልጣንወንበራቸውን የሚነካ ነገር አብይ አህመድ ጣል ሲያደርግ ብቻ ነበር።

አብይ አህመድ ለተነሱት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ከመስጠት ይልቅ ሁሉንም የሚያሸማቅቅና የሚያሸብር መልእክት አስተላልፏል።ስለአማራው እልቂትና ጦርነት የምታነሱ አርፋችሁ ተቀመጡ በማለት ጸጥ ለማድረግ ሞክሯል።ብልጽግና ከተተከሎ ቀሮችና ከወያኔ ተላላኪዎች እራሱን አጽድቶ በመሠረታዊ ፓርቲነት ይቀጥላልም ብሏል።ከተተከሉ ቀሮችና የወያኔ ተላላኪዎች ሲል በተቃዋሚነት በተለይም ስለ አማራው ያገባናል የሚሉትን ከብልጽግናም ውጭ ያሉትን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። በዚህ አይነቱ ስድብ፣ንቀትና እብሪት እንዲሁም ውዥንብርና ፍርሃት በዋጠው ስብሰባ መጠናቀቂያ አብይ አህመድ የብልጽግናን ዓላማ በግልጽ  አስቀምጧል።

ካስቀመጣቸውም ዋና ዋና ነጥቦች

1 ላለፉት 30 ዓመታት በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት እንደማይነካ፣

2, አዲስ አበባ ፊንፊኔ ተብሎ መጠራት እንዳለበት፣

3/የኢሕአዴግ ባንዲራ እንደማይቀዬር፣

4 የክልል አወቃቀሩ እንደሚቀጥል፣

5/ የመሬት ጉዳይ ሕገመንግሥታዊ ስለሆነ በሕገመንግሥቱ መሠረት ተከብሮ እንደሚቀጥል

ከነዚህን አንኳር ነጥቦች ስንነሳ የኦሕዴድ -ኦነግ መራሹ ብልጽግና የወያኔ ግልባጭ ተረኛ እንጂ  ከወያኔ አለመለዬቱን  ያረጋግጣል።ብልጽግናን የተለዬና የተሻለ፣ኢትዮጵያን የሚያሻግር አድርገው  የሚያዩትንና ከበሮ የሚደልቁትን ሆድ አደሮች ዓይናችሁን ግለጡ እንላለን።በያዙት መንገድ እንቀጥልበታለን ካሉም ምርጫቸው ነው።ግን ከጥፋት ተጠያቂነት እንደማያመልጡ ሊያውቁት ይገባል። እንደለመዱት ኮፍያ

እዬቀያየሩ ከመጣው ጋር ለማወናበድ የሚችሉበት ዕድል ወደ ፊት አይኖርምና ካሁኑ እርማችሁን አውጡ እንላቸዋለን።

ከስብሰባው ዓላማ ስንነሳ ብልጽግና የሚባለው ስብስብ መፈራረሱ የማይቀር ሆኖ እናዬዋለን።በብአዴን ውስጥ የሚነሳው ሽኩቻ በቀላሉ የሚበርድ አይመስልም። በሰረቁትና ለመስረቅ ባልቻሉት መካከል ፍጭቱ ንሯል።ድርጅቱ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል። በዚያ ላይ የሕዝቡ ተቃውሞ ሲጨመርበት የመቀጠሉ ዕድሉ የመነመነ ይሆናል።ከሰረቁት መካከል 16ቱ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲመልሱና ከተቀመጡበት ሃላፊነት እንዲነሱ ብአዴን ወስኗል።የሚገርመው ከፍተኛ ገንዘብ ሰርቀዋል የተባሉት እነ አገኘሁ ተሻገር አለመነካታቸው ነው።ከ300 ሽህ ጀምሮ የተቀራመቱት አደራ በሌዎች የመጨረሻቸው ምን እንደሚሆን ባይታወቅም በሕግ መጠዬቅ አለባቸው እንላለን።በብአዴን የተነሳው ውዝግብ በራሱ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ለአጠቃላዩ ብልጽግና ተብዬውም መፈራረስ ምክንያት ይሆናል።ያ ከሆነ በኦነጋውያንና በወያኔ ታቅዶ ሲሠራበት የቆዬው አገር የማፈራረሱን ዓላማ ያፋጥነዋል ማለት ነው። ኢትዮጵያ በብልጽግና የተገነባች አገር አይደለችም፤በብልጽግና ፍላጎትም ልትፈርስ አይገባም። ለማንኛውም ለመሰብሰብ ከቻለ ከቀናት በኋላ የሚሰበሰበው ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ምን ሊሆን እንደሚችል የምናዬው ይሆናል።ለከፉም ሆነ ለበጎ እራስን አዘጋጅቶ መጠበቅ ተገቢ ነው። በቀላሉ አገር እንደ ዳቦ ቆራርሶ መቀራመት አይቻልም።የኢትዮጵያውያን ታሪክ አገራችንን አሳልፎ የመስጠት ስላልሆነ እስከመጨረሻው ድረስ ለመታገል መዘጋጀት ይጠበቅብናል።

ወደ ማክሰኞና ዕሮብ ስናመራ ትልቁ እርዕስ የአድዋ ድል የ126ኛው ዓመት አከባበርን የሚመለከት ይሆናል። በበዓሉ ዋዜማ ማክሰኞ ዕለት፣ ስለ በዓሉ አከባበር ከባህልና እስፖርት ሚኒስትሩ ከኦነጉ ከቀጀላ መርዳሳ የተሰጠው መግለጫ በዓሉ በየዓመቱ በሚከበርበት በዳግማዊ ምኒሊክ አደባባይ መሆኑ ቀርቶ በአድዋ ድልድይ ወንዝ ዳር እንደሚከበር የሚገልጽ ነበር።ይህንን መግለጫ የሰማው ሁሉ ከዳር እስከዳር በቁጣ ተቃውሞውን አሰምቷል።በቁጣው መጠናከር የተደናገጠው የብልጽግና አመራር የሕዝቡን ቁጣና ተቃውሞ ለማለዘብ ሲል በአማራዋ የብልጽግና ተላላኪ በሂሩት ካሣው በኩል ሌላ መግለጫ ይዞ ብቅ አለ።በዓሉ በምኒሊክ አደባባይ ተጀምሮ በአድዋ ድልድይ የሚከበርና የሚጠናቀቅ መሆኑን ተናገረች።የችግሩ ምክንያትም መግለጫውን ሙሉ ለሙሉ ካለማስተላለፍ የመጣ ስህተት ነው በማለት ላሙኛችሁ ዓይናችሁን ጨፍኑ በሚል መልኩ ለማስተባበል ብትሞክርም የሕዝቡን ንዴት ሊያበርደው አልቻለም።ሌሊቱኑ ሲንገበገብ ያደረው አዲስ አበቤ ወፍ ሳይጮህ በማለዳ የኢትዮጵያን ነባር ሰንደቅ ዓላማ አንግቦ ከያቅጣጫው ጎርፎ የምንሊክ አደባባይንና አካባቢውን አጥለቀለቀው።

በከተማዋ ታይቶ ተሰምቶ በማያውቅ የሕዝብ ብዛት ሲከበር ይህ የመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ የተነገረለት የአድዋ ድል በዓል አከባበር መንግሥት እንዳሰበው ሳይሆን ሕዝቡ በመረጠውና በፈለገው መንገድ ተከብሮ ውሏል። ለመቆጣጠር የከተማው አስተዳደር ከኦሮሚያ ክልል ተብዬው ጋር በመተባበር ቁጥር ስፍር የሌለው የፖሊስና የጸጥታ ሃይል ቢያሰልፍም የአዲስ አበባ ኑዋሪ በተለይም ወጣቱ ደረማምሶት ማለፉ ብቻ ሳይሆን የፖሊስ ሃይሉ በሕዝቡ በመዋጡ በከባቢው መኖሩም ያልታዬበት ነው። ኦነጋውያኑን የሚያስፈራውና ሲያስቡት ቅዠት የሚለቅባቸው ልሙጡ ሰንደቅ ዓላማ ከተማዋን አጥለቅልቋት ውሏል።መዝሙሩ፣ ፉከራና ሽለላው፣የኪነቱ ቅንብር ከፈጠረው የወኔ ስሜት ጋር ሲታይ ዳግም አድዋ የተከሰተ አስመስሎታል።ምንሊክና ጣይቱ ጠሌ የሆነችው የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አበቤም ሆነች የባህልና የስፖርት ሚኒስትር ተብዬው ቀጀላ መርዳሳ በምኒሊክ ሃውልት ስር አበባ የማስቀመጥ ሃላፊነት ቢኖርባቸውም፣ካላቸው ጥላቻና ፍርሃት የተነሳ በከባቢው ለመታዬት ድፍረት አጥተው በተላላኪዎቻቸው በኩል አስፈጽመዋል።

በዓሉ በሁለት ቦታዎች የተከበረ ሲሆን ምልአተ ሕዝቡ ላለፉት 119 ዓመታት ሲከበርበት በኖረው በዳግማዊ ምኒሊክ አደባባይ ፣ የሥርዓቱ ባለስልጣኖችና አጃቢዎቻቸው በአድዋ ድልድይ ባለው ወንዝ ዳር ነበር።በድልድዩ አጠገብ በተተከለው ድንኳን የተገኙት የመንግሥት ተወካዮች በተለይም ፕሬዚደንት ተብዬዋ አንድም ጊዜ የድሉን ባለቤቶች የምንሊክንና የእቴጌ ጣይቱን ስም ለማንሳት አልደፈሩም። ቀጀላ መርዳሳን ወክላ በቦታው የተገኘችው የኦሕዴዱ የባሕልና ቱሪስት ሚኒስትር ዴታ ባደረገችው ንግግሯ ያወሳቻቸው በአድዋ የነበሩትን መሪዎችና አርበኞች ሳይሆን የኦሮሞ ፈረሶችንና ፣ ከዚያም ከበዓሉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን የዘፋኝ ሃጫሉ ሁንዴሳን ስም እያነሳች ነበር። ያቀረበችው ንግግር እሷን ብቻ ሳይሆን የላካትን የኦሕዴድ -ኦነግ ቡድን መሪ አብይ አህመድንና ድርጅቱን ጭምር ያጋለጠና r አሳፋሪ ነበር።የእምዬ ምኒሊክንና እቴግ ጣይቱ ብጡል ስም በኦነጋውያን ባይነሳም የጀግኖቹን መሪዎች ስምና ዝና የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የጥቁር ሕዝብ በመላ ነጮቹም ሳይቀሩ የሚያወድሱት ነው። መከበር ሪያና መታፈሪያ ለኦነጋውያን ቀረባቸው እንጂ ለነምኒሊክ የቀረባቸው የለም።ህሊና ያለው ሰው እንዴት የባርነት ሰንሰለት ይናፍቀዋል?እንዴትስ በባርነት ሰንሰለት እንዳይታሰር ያደረገውን ባለውለታ መሪውን ይጠላል?እንደሌላው አፍሪካዊ የነጮች የባርነት ቀንበር ተሸክሞ በየጥጥ ማሳው እየተገረፈ መሥራቱ ቀረብኝ ብሎ ነጻነትን መጥላት ከምን የመጣ በሽታ ነው? ይህንን ኦነጋውያንና ወያኔዎች መልስ ይስጡበት።

ሕዝቡ በሁለቱም ቦታዎች የበላይነቱን አሳይቶ ውሏል።በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የታጀበው ክብረበዓል የኢትዮጵያን ትንሳኤ ያበሰረ መሆኑን ብዙዎች በደስታ ገልጸውታል።እኛም በአካል ባይሆንም በዜና ስርጭት እንደተከታተልነው እውነትም ኢትዮጵያዊነት ያሸነፈበት እለት ነበር።ዝም ያለ ሕዝብ ፈሪና ጅል አለመሆኑን ያዩት ትእቢት የወጠራቸውና ያሳበዳቸው ተረኞች ከብልግናቸው እንዲታቀቡ ያደርጋቸዋል የሚል እምነት ባይኖረንም በያዙት ከቀጠሉበት በጣልያኖች ላይ ያረፈው የአድዋ ዱላ በነሱም ላይ ሊያርፍ እንደሚችል ይገነዘቡታል ብለን እናምናለን። ሕዝብ ከተባበረ የሚያቆመው ምድራዊ ሃይል እንደማይኖር የታዬበት ዕለት ነበር።

ቀጀላ መርዳሳ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በሰጠው ኢንተርቪው ኦሮሞን የጨፈጨፈው ምኒልክና አማራ ነው በማለት የወነጀለ ሲሆን፤በባንዲራውም ላይ ያለው ቢጫ ቀለም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምልክት ነው በማለት አጣጥሎት ነበር።በራሱ በኦነግ ባንዲራ ላይ ያለውን ቢጫ ቀለም ሲጠየቅ ግን የተለዬ መንፈሳዊ ትርጉም ሰጥቶታል። እንዲህ አይነቱ ወራዳ በአድዋ በዓልና በምንሊክ ላይ ጥላቻ ቢኖረው ምን ያስገርማል?የሚያስገርመው ግን አሁን ሥልጣን ሲሰጠው የሚጠላውን ባንዲራ ከነአምባሻው መሸከሙና በቢሮ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ዓይን ዓይኑን ማዬቱ ነው።

የአዲስ አበባ ነዋሪ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ከመዝሙርና ጭፈራው ቀጥሎ ለወሳኙ ትግል መሰናዳት እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።አዲስ አበባን የመዋጡ፣ብሎም ኢትዮጵያን የመቀራመቱ እቅድ ተነድፎ በተግባር ሊገለጽ ያለው ዕድሜ በጣም አጭር ነው።ፊንፊኔ የሚለው ስያሜ በመንግሥት ተብዬው እዬጎላ መምጣቱ፣የወልቃይትንና ራያን እንዲሁም የአፋርን መሬት ለወያኔ ተደራድሮ አሳልፎ ለመስጠት አማራውንና አፋሩን ለማጥቃትና ለማስጠቃት መወሰኑ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤ ለመጨረሻው ግብ የመንደርደሪያ እርከን ነው። ስለሆነም ያለው አማራጭ አንድና አንድ ነው።በከተማና በገጠር ሕዝባዊ ሃይሉን አደራጅቶ ትግሉን ማጠናከር ነው።ሕዝባዊ ትግሉን ለማዳከም ሰርጎ ገቦችን ማሰማራት አንዱ የገዢው ቡድን ስልት ስለሆነም ትልቅ ጥንቃቄና መናበብ ያስፈልጋል። ለሕዝቡ የቆሙትንም በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ያሉትንም ጭምር መጠበቅና ከአደጋ መከላከል የሁሉም አገር ወዳድ ሓላፊነት ነው። በብዙ መረጃ ሊረዱ ይችላሉ። በጎጥና መንደር፣በሃይማኖትና በጾታ ለመለያዬት የሚሸረብም ተንኮል ስላለ ከወጥመዱ ላለመግባት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።የፖለቲካ

ልዩነት ቢኖር ከድል በኋላ የሚታይ እንጂ ከድል በፊት የሚለያይ ጉዳይ መሆን አይኖርበትም። መጀመሪያ የመቀመጫዬን እንዳለችው መጀመሪያ የምንኖርበትን አገር ማስከበር ነው።አገር አጥፊው ቡድን ሲያጠፋ ሃይማኖትና ጾታ ለይቶ ሳይሆን በማንነቱና በሚናገረው ቋንቋ ነው።ሌላውን አጥፍቶ እኔን ይምረኛል የሚል ሃሳብ መኖር የለበትም።እሱን ያልሆነውን ሁሉ እንደሚያጠፋው ከአሰላለፉ፣ ከፈጸመውና ለመፈጸም ከሚጎሸመው የጥፋት ነጋሪት መረዳት ይቻላል።

በአለፈው ሃሙስና አርብ የተሰማው አሳዛኝ ድርጊት በዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ በሚማሩ በሽህ በሚቆጠሩ ተማሪዎች ላይ ጥቃት መድረሱ ነው። የአድዋን በዓል አስመልክቶ የከባቢው ነዋሪና የኦሮሞ ተወላጆች የሆኑ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በጥምረት ባካሄዱት ጥቃት አማራ የሆኑትን እዬለዩ በዱላና በቆንጨራ እያሳደዱ ብዙ ተማሪዎች እንደሞቱና እንደቆሰሉ የወጣው መረጃ ያረጋግጣል።ህይወታቸውን ለማትረፍም ብዙዎች ጫካ ገብተው ድረሱልን እያሉ መሆናቸው ተሰምቷል።የከባቢው አስተዳደርም ሆነ የመከላከያ ሃይል ሊታደጋቸው ፈቃደኛ አልሆነም።በዚሁ በወለጋ ውስጥ ከ125 በላይ የአማራ ተወላጆች በታጠቁ ሃይሎች መገደላቸው ይፋ ሆኗል።በግድያው ላይ የከባቢው የጸጥታ አባላትም እንደተሳተፉበት የወጣው መረጃ ያረጋግጣል።

በቤን ሻንጉል ክልላዊ አስተዳደር ውስጥ የሚንቀሳቀሱት የወያኔ፣ጉምዝና የኦነግ አሸባሪ ቡድኖች በወሰዱት የማጥቃት እርምጃ ከመቶ በላይ የህዳሴው ግድብ ሠራተኞችና የጥበቃ አባላት መገደላቸው ይፋ ሆኗል።ጥቃቱ የተፈጸመው ሠራተኞቹ በጉዞ ላይ በነበሩበት ወቅት ነው። በጥቃቱ ከሃያ በላይ ተሽከርካሪዎች ተቃጥለዋል።መንገድና ከባቢውን ከአሸባሪዎች ነጻ ማድረግና በተለይም የግድቡንና የሠራተኞችን ደህንነት ማስከበር የክልሉ አመራር አላፊነት ቢሆንም ካለው የጥቅምና የአቋም አንድነት ተደጋጋሚ ጥቃት ሲፈጸም ከማዬት ባለፈ በአሸባሪዎች ላይ እርምጃ ሲወስድ አልታዬም፣ ይወስዳል ተብሎም አይጠበቅም።ይህ አይነቱ የጥቃት እርምጃ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፤የመጨረሻም አይሆንም። አገር አፍራሹ የጎሳ ፖለቲካ እስካለ ድረስ ፣ኢትዮጵያዊው በሚገባ ተደራጅቶ መከላከል ብቻ ሳይሆን መቆጣጠር ከሚችልበት ቁመና ላይ ካልደረሰ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ወደ ቀጣዩ እርዕስ ስናመራ ፣የኦነግ መራሹ ኦሕዴድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን በቁጥጥሩ ስር ካደረገ ጀምሮ በከተማዋና በከተማው ንዋሪ ላይ የሚያደርሰው በደል ከቀን ወደ ቀን እያደገ መጥቷል። የከተማውን ነዋሪ ለማፈናቀል ሲል ገዝቶና ወርሶ ለብዙ ዓመታት የኖረበትን የከተማ ቦታ የመንግሥት ይዞታ በማድረግ ከፍተኛ የሊዝ ተመን ጥሎ እዬዘረፈው ይገኛል።በጣም የሚገርመው ከዓመታት በፊት የተገዙ ቦታዎች ላይ የአሁኑን የዋጋ ተመን በመጣል የሊዝ ክፍያ እንዲከፍሉ ማስገደዱ ነው።የቻለ ይከፍላል፣ያልቻለ ይነጠቃል። ነገሩን አስቂኝ የሚያደርገው የዛሬ አስር ዓመት ከጋራጅ የገዙትን መኪና ከአሥር ዓመት በኋላ ባለጋራጁ መጥቶ በዛሬው የዋጋ ተመን ክፈለኝ ብሎ የመጠዬቅ ያህል መሆኑ ነው።በዬትኛውም ዓለም እንዲህ ያለ የገበያም ሆነ የሊዝ ውል የለም።ነባሩ ውል ሲያልቅና አዲስ ውል ሲፈረም ብቻ በተፈረመበት ጊዜ ባለው ተመን ሊሆን የሚችልበት አሠራር ነው።

ሌላው አሳሳቢ ሰሞንኛ ጉዳይ የኦነግ- ኦሕዴዱ ቡድን የኢትዮጵያን በተለይም የአዲስ አበባን ታሪክና ቅርስ የማውደሙን ሥራ መቀጠሉ ነው።በዓለም አቀፍ ደረጃ በቅርስነት የተመዘገቡ ተቋማትን፣ ሕንጻዎችን ፣የእጅ ሥራ ጥበቦችን ተንከባክቦ ለትውልድ የማድረስ በሕግ የተደነገገ ሃላፊነት እንዳለ የሚታወቅ ነው።ኢትዮጵያም የዚህ ውል ፈራሚ ነች።በሥልጣን ላይ ያለው ጭፍን አገር አጥፊ ቡድን የአገሪቱንና የከተማዋን ታሪክ መስካሪ ገጾችንና ቅርሶች የማጥፋት ዘመቻውን ከከፈተ የቆዬ ቢሆንም አሁን በአዲስ ጉልበት ተነስቶበታል።በታደሉት አገሮች ያለፉ ታሪኮች መዝገብ የሆኑ ተቋማትና የሥራ ውጤቶች በክብርና በፍቅር ተንከባክበው የሚያዙ ናቸው። ካለነዚያ የአገር ታሪክ አብሳሪዎች ተተኪው ትውልድ ሊኮራበት የሚችልበት ብሔራዊ ስሜት አልባ ይሆናል።የወደፊቱን የሚያይበትና

የሚመትርበት ያለፈው ትውልድ ጠብቆ ያስረከበው ታሪክና ቅርሶች ሲኖሩት ነው።ካለትናንትናው ዛሬ፣ካለዛሬው ነገም አይኖርም።

በዓለም አቀፉ መመሪያ በቅርሳዊ ሕንጻ ላይ ሌላው ቀርቶ አስፈላጊነቱ በጠቢባን ታምኖበት፣ ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ለማሶገድ ካልሆነ በስተቀር አንዲት ሚስማር ልትመታ ወይም ልትነቀል አይፈቀድም።በእኛ አገር ግን ችግር የለውም።ስለቅርስና ታሪክ ግንዛቤ የሌለው ጊዜ ያነሳው አገር ጠሌ የሥልጣኑ ማሳያ የሚያደርገው በሚጠላው አገር ታሪክና ንብረት ላይ የሚወስደው የጥፋት እርምጃ ነው። ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ነውና የአውዳሚዎቹን እንቅስቃሴ በመግታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአዲስ አበባ ነዋሪ ካለፈው ትውልድ የተረከበውን ቅርስና ታሪክ አስከብሮና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ የማስረከብ አላፊነቱን እንዲወጣ ጥሪ እናደርጋለን። በእድሳትና በግንባታ ስም ብዙ ታሪካዊ ቅርሶች ወድመዋል።ሌሎች እንዳይወድሙ በንቃት መጠበቅ የትውልዱ ሃላፊነት ነው።

ወደ ዓለም አቀፉ የሰሞኑ ጉዳይ ስናልፍ አሁንም መድረኩን ያጣበበው በሩስያና በኡክሬን መካከል የሚካሄደው ጦርነት ነው።ማንኛውም ጤነኛ አይምሮ ያለው ሰው ጦርነትን አይወድም፣አይደግፍም። ለጦርነት መነሻ ምክንያት ፣ተገፊና ገፊ፣ቀስቃሽና ተከላካይ መኖሩ አይካድም። በጦርነት ምክንያት አገር ይወድማል፣ሕዝብ ያልቃል፣ይሰደዳል። ጦርነትን መጀመር ይቀላል፤ማቆሙ ግን ከባድ ይሆናል። ከሁሉም የሚያዋጣው መፍትሔ ግን ለጦርነት የሚያበቃውን ምክንያት ለማሶገድ ጥረት ማድረግ ነው። በኡክሬኑ ጦርነት ከሚሊዮን በላይ ሕዝብ ከቤቱ ወጥቶ በየገሩ ለመሰደድ ተገዷል።ከነዚያም ውስጥ ለትምህርትና ለሥራ ኡክሬን ውስጥ የሚኖሩ አፍሪካውያን ይገኙበታል።እነሱም እንደ ሕዝቡ ህይወታቸውን ለማትረፍ ወደ ጎረቤት አገራት ለመሰደድ ተገደዋል።ለሁሉም እኩል በመጣው መከራ ላይ አፍሪካውያኑ ሌላ ተጨማሪ መከራ እንዲደርስባቸው ሆነዋል።በቆዳ ቀለማቸው ምክንያት ከሚሳፈሩበት አውቶብስ ወይም ባቡር ቅድሚያ ለነጭ ነው በመባል እንዲወርዱ ይገደዳሉ። እንደምንም ብለው ጎረቤት አገር ድንበር ላይ ሲደርሱ የድንበር ጠባቂዎች እዬነጠሉ መግባት ይከለክሏቸዋል፤ያም ብቻ አይደለም ስብእና በሚነካ መልኩ ይሰድቧቸዋል፤ይደበድቧቸዋል። በመንገድ መንገላታትና በክረምቱ ብርድ ላይ ይህ ሲጨመርበት መፈጠርን ያስጠላል። በአጠቃላይ ሲታይ አውሮፓ ከዘረኛነት ያልተላቀቀች መሆኗን ለማዬት ተችሏል። ስደትም የዘር ልዩነት የሚስተናገድበት ሆኖ ታይቷል።የአፍሪካ መንግሥታት እነዚህን ዜጎቻቸውን ከመከራ የማውጣትና ሰብአዊ ክብራቸው እንዳይደፈር የመከላከል ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው።ሌላውም አፍሪካዊ በነዚህ አፍሪካውያን ላይ የሚደርሰውን በደል ማጋለጥና መቃወም ይጠበቅበታል። በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድና በአሜሪካ የነጮች የበላይነት ጊዜ የነበረውን ግፍ የደገመ ድርጊት ነው። ጦርነቱ ከቀጠለና ሌላ መልክ ከያዘ በአውሮፓ የሚኖረው አፍሪካዊ ወይም የተለዬ የቆዳ ቀለም ያለው ምን ሊደርስበት እንደሚችል ይህ አመላካች ነው።የሁለተኛው ዓለም ጦርነትን ማሰቡም ለጥንቃቄ ይረዳል። በጣም አሚገርመው ደግሞ በሴኔጋል የሚገኘው የኡክሬን ኤምባሲ አፍሪካውያን በቅጥር መልክ እንዲዋጉለት ያወጣው ማስታወቂያ ነው።ይህንን ንቀትና ድፍረት ብዙ ያፍሪካ አገሮች አውግዘውታል፤የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ያለው የለም።

ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ስንመለስ በየካቲት 26 ቀን በሚከበረው የካራማራ ድል ምክንያት ጥቂት የአዲስ አበባ ወጣቶችና የባልደራስ ፓርቲ መሪዎች በዓሉን ለማክበር አደባባይ ወጥተው ነበር። የከተማዋ አስተዳደር የፖሊስ ሃይል በማሰማራት ለማስቆም የሞከረ ቢሆንም ፍጹም ሰላማዊ የሆነው ሰልፈኛ ካሰበው ቦታ ደርሶ ለበዓሉ የሚስማሙ መዝሙሮችን ከማሰማት አልተመለሰም። ባልተዋጠላቸው ባለሥልጣኖች ትዕዛዝ ከሰላሳ የማያንሱት ሰልፈኞች በፖሊስ መኪና ተጭነው ወደ

ልደታ ፖሊስ መምሪያ ከተወሰዱ በኋላ ሌሎቹ ሲቀሩ የባልደራስ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ እስክንድር ነጋ ተለቋል።የሌሎቹ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል የታወቀ ነገር የለም።ምናልባትም እንደተለመደው በገንዘብ ዋስትና ሊለቀቁ ይችሉ ይሆናል። ይህ ከአርባ አምስት ዓመት በፊት የሶማሊያን የመስፋፋት ወረራ፣ በሶቪዬት ጀነራሎች የጦር እቅድ፣በኩባና በየመን ሜካናይዝድ ጦር ተሳትፎ፣በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በተለይም በኢትዮጵያ አዬር ሃይል ጀግንነት የተገኘ ድል በአገር ጠሎቹ ህዋህታውያኑና ኦነጋውያኑ ትኩረት እንዳያገኝ የተደረገ ብሔራዊ ድል ነው።በታላቅ ዝግጅት ሊከበር ይገባዋል።

የአድዋን በዓል ተከትሎም በዓሉን ያስተባበሩትና  ድምቀት የሰጡት ወጣቶች እዬታደኑ መሆናቸው ታውቋል።ኢትዮጵያ ጠል የሆነው ኦነግ መራሹ ቡድን  የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሲያይ ዛሩ ይነሳል፤ ያንቀጠቅጠዋል።ጠቡ ከወጣቱ ጋር ሳይሆን ወጣቱ ከያዘው ሰንደቅና ከሚያንጸባርቀው ኢትዮጵያዊነት ጋር ነው።

ኢትዮጵያ  በተለይም የአዲስ አበባ ሕዝብ ይህንን የመንግሥት እኩይ ተግባር ሳይቃወም ልጆቹን ለአደጋ አጋልጦና አሳልፎ ከሰጠ ታሪክ ይቅር የማይለው ጥፋት የፈጸመ  መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል። ስለሆነም ትግሉን  ተቀላቅሎ ማፋፋም ይጠበቅበታል።

አገራችንን ከተደቀነባት አደጋ ይሰውራት፤ዓለማችን ላይ ሰላም ይስፈን!

ኢትዮጵያ ፣በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!